# ሰሜን ምስራቅ 130ኛ ጎዳና እና ሰሜን ምስራቅ 125ኛ ጎዳና ተንቀሳቃሽነት እና ደህንነት ፕሮጀክት

መስከረም 2023




## ከቀላል ባቡር እና ከሰፈርዎ ጋር ግንኙነቶችን ማሻሻል!

በ 2026፣ ሳውንድ ትራንዚት ከI-5 አቅራቢያ ያለውን የ NE 130th St ቀላል ባቡር ጣቢያ ይከፍታል እና በየቀኑ ከ3,300-3,700 ተሳፋሪዎችን ይጠብቃል - 90% ተሳፋሪዎች በእግር ፣ በብስክሌት ወይም በህዝብ መጓጓዣ ይደርሳሉ። ያቀድናቸው ማሻሻያዎች ለእግረኛ፣ ለቢስክሌት፣ ለሚንከባለሉ እና በአውቶቡስ ለሚጓዙ ሰዎች ወደ አዲሱ ቀላል ባቡር ጣቢያ ለመድረስ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀላል ያደርገዋል። ቡድናችን በNE 130th St፣ Roosevelt Way NE እና NE 125th St በ1st Ave NE እና Lake City Way NE መካከል ማሻሻያዎችን እየነደፈ ነው።

የፕሮጀክት ማሻሻያዎች የሚያካትቱአቸው:-

- በፕሮጀክቱ አካባቢ በሙሉ የተጠበቁ የብስክሌት መስመሮች
- ድግግሞሽ እና አስተማማኝነትን ለማሻሻል እንደ አዲስ ወይም የተሻሻሉ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች እና ቅድሚያ የሚሰጠው የአውቶቡስ ባህሪያት ያሉ የመጓጓዣ ማሻሻያዎች
- ገዳይ እና ከባድ የአካል ጉዳቶችን ለመቀነስ የመንገድ እና መገናኛ ንድፎችን ማዘመን
- የሚራመዱ እና የሚንከባለሉ ሰዎች ቅድመ መረጃ ለመስጣት እንደ ጠቋሚ የእግረኛ ክፍተቶችን ያሉ የማቋረጫ ማሻሻያዎች
- የእግረኛ መንገድ ጥገና እና አዲስ ተደራሽ ከርብ ራምፕስ በተመረጡ ቦታዎች

**የእኛን ድረ-ገጽ ለመጎብኘት እና የግብረ መልስ ቅጹን ለመሙላት ከታች ያለውን የQR ኮድ ይቃኙ።** የእርስዎ ምላሾች አሁን እና ወደፊት የማህበረሰብ ፍላጎቶችን በተሻለ ሁኔታ እንድንረዳ ይረዱናል።

**እኛ የሚከተሉትን ማወቅ እንፈልጋለን:**

- በሰፈሩ ውስጥ እንዴት እንደሚጓዙ
- NE 130th St ቀላል ባቡር ጣቢያ ሲከፈት ጉዞዎ እንዴት ሊለወጥ እንደምችል
- ስለ ቀደምት የዲዛይን ፕሮፖዛሎቻችን ምን ያስባሉ


**የፕሮጀክት አድራሻ/ግንኙነት:**
ድሩ ንየንሁይስ
NE130thSt_NE125thSt_Project@seattle.gov
(206) 400-7515
www.seattle.gov/transportation/NE130thMobilityProject



Seattle Department of Transportation
King County METRO

# የፕሮጀክት የጊዜ መስመር:

| PLANNING | | DESIGN | | CONSTRUCTION | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| Master Plan(s) | Project Development | Early Design | Final Design | Pre-construction | During | Wrap-up |

we are here

- **እቅድ ማውጣት (የተጠናቀቀ):** ቀደም ሲል በአካባቢው የተሰሩ የዕቅድ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ስራዎችን ለማጠናከር ከማህበረሰብ አባላት እና ከንግድ ባለቤቶች ጋር ተነጋግረናል። የእኛ ስራ የደህንነት እና የተደራሽነት ማሻሻያዎችን በፍትሃዊነት እና ባለው የገንዘብ ድጋፍ መንደፍ ያካትታል።

- **ንድፍ (2024-2025):** የፕሮጀክት ዲዛይን ፕሮፖዛሎችን እንፈጥራለን እና እንካፈላለን፣ የማህበረሰብ አስተያየት እንጠይቃለን እና የፕሮጀክት ዲዛይን እናጠናቅቃለን።

- **ግንባታ (2025-2026*):** እዚህ ደረጃ ላይ ስንደርስ ስለ ግንባታ መርሃ ግብሮች፣ እንቅስቃሴዎች እና የሰፈር ተጽእኖዎች የበለጠ መረጃ እናካፍላለን።

- **የቀላል ባቡር አገልግሎት (2026) ይጀምራል:** የሳውንድ ትራንዚት የሰሜን ምስራቅ 130ኛ ጎዳና ማስገቢያ ጣቢያን ለመክፈት እና በ2026 አገልግሎቱን ለመጀመር አቅዷል። እባክዎን ለአሁኑ የጊዜ ሰሌዳ እና የፕሮጀክት መረጃ የSound Transit ድህረ ገጽን ይጎብኙ።

የግንባታ መርሃ ግብሮች በሠራተኞች እና በቁሳቁስ አቅርቦት ላይ በመመስረት ሊለወጡ ይችላሉ።

**የፕሮጀክት አድራሻ/ግንኙነት:**
ድሩ ንየንሁይስ
NE130thSt_NE125thSt_Project@seattle.gov
(206) 400-7515
www.seattle.gov/transportation/NE130thMobilityProject

Seattle Department of Transportation
King County METRO